

# የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ክፍል ሁለት/2

ግርማ ሞገስ (girmamoges1@gmail.com)

እሁድ መስከረም 12 ቀን 2006 ዓ.ም. (September 22, 2013)

በክፍል አንድ እንዳነበብነው የዝንጀሮዎቹ አምባገነን ጌታ ተርቦ ከመሞቱ በፊት የሚቀልቡት የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ነበሩት። የፖለቲካ ኃይል ምንጮቹ መድረቅ ተርቦ እንዲሞት አድርገውታል። እንደ ዝንጀሮዎቹ አምባገነን ጌታ መንግስትም የፖለቲካ ኃይል ምንጮች አሉት። የአንድ መንግስት የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ከሞላ ጎደል የሚከተሉትን ያካትታል። (1) መንግስት ከህዝብ የሚያገኘው የገዢነት ክብር፣ ህጋዊነት፣ (2) መንግስት ከቢሮክራሲው (ከመንግስት ሰራተኞች) የሚያገኘው ትብብር መጠን፣ (3) መንግስት ከሙያተኞች የሚያገኘው የቴክኖሎጂ ክህሎት እና ፕላን የማቀድ፣ የማስተዳደር እና የመሳሰለው ዕውቀት ትብብር፣ (4) የመንግስት የአገር ኢኮኖሚ (የተፈጥሮ ሃብት፣ የገንዘብ፣ የኢንዱስትሪ፣ የእርሻ፣ የንግድ፣ የትራንስፖርት፣ የኮምኒኬሽን) ባለቤትነት፣ (5) በመንግስት ስልጣን ላይ የሚገኙ መሪዎች በሚከተሉት ርዕዮተ ዓለም ወይንም በጎሳ ማንነታቸው የሚያገኙት የተወሰነ ህዝብ ክፍል ድጋፍ፣ (6) በመጨቆኛ እና በመቅጫ ተቋም ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራው ፖሊስ፣ ደህንነት እና የጦር ኃይል ለመንግስት የሚለግሰው ትብብር።

እንደሚታወቀው 200 ያህል የሰላም ትግል ማራመጃ መሳሪያዎች (Weapons) አሉ። እነዚህ መሳሪያዎች በሶስት አብይ ክፍሎች ይከፈላሉ። እነሱም (1ኛ) ተቃውሞና ማግባባት (Protest and Persuasion)፣ (2ኛ) ትብብር መንፈግ (non-cooperation) እና (3ኛ) ጣልቃ መግባት (intervention) ይባላሉ። ዛሬ በኢትዮጵያ "እየሞትን ሳንገድል ህገ-መንግስት እናስከብራለን" በሚል መርህ አንድነት ፓርቲ ከሰኔ ወር 2005 ዓ.ም. ጀምሮ በአገር አቀፍ ደረጃ ሲያኪያሂድ የነበረው እና መስከረም 19 ቀን 2006 ዓ.ም. በመስቀል አደባባይ የሚያጠናቅቀው "የሚሊዮኖች ድምጽ ለነፃነት" የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፎች፣ ፊርማ የማሰባሰብ እና ህዝባዊ ስብሰባዎች የማድረግ ዘመቻዎች (1ኛ) ተቃውሞና ማግባባት (Protest and Persuasion) ለሚለው የሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያ ጥሩ ምሳሌ ነው።

የዝንጀሮዎቹ ትብብር መንፈግ (Non-cooperation) ለረጅም ጊዜ የተደላደለውን የዝንጀሮዎቹን አምባገነናዊ ጌታ የገዢነት ስልጣን (የፖለቲካ ኃይል) ምንጭ እንዳደረቀ እና ከትከሻቸው ላይ አሽቀንጥሮ እንደጣለላቸው በክፍል አንድ አይተናል። ስለዚህ የተለገሰን ትብብር መሉ በሙሉ መሳብ (መንፈግ) ይቻላል። በዚህ ክፍል ደግሞ ከፍ ብለው የተዘረዘሩትን የመንግስት የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ለማድረቅ ሰላማዊ ትግል ከሚጠቀምባቸው 200 ያህል የሰላም ትግል ማራመጃ መሳሪያዎች ውስጥ ትብብር መንፈግ (Non-cooperation) ምን ምን አይነት እርምጃዎችን እንደሚያካትት እና አቅሙ ምን ያህል እንደሆነ እንመረምራለን። እግረ መንገዴን (3ኛ) ጣልቃ መግባት (intervention) የተባለውን የሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያ ባጭሩ አቀርባለሁ።

ትብብር መንፈግ ሲባል ፖለቲካዊ ትብብር መንፈግ (Political Non-cooperation) ወይንም ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈግ (Economic Non-cooperation) ወይንም ማህበራዊ ትብብር መንፈግ (Social Non-cooperation) ወይንም ሁሉቱ ብቻ ወይንም ሶስቱም ማለት ሊሆን ይችላል። ትብብር መንፈግ የመንግስትን የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ለመቆጣጠር እና መንግስት ለህዝብ ጥያቄ መልስ እንዲሰጥ ለማድረግ ይጠቅማል። አልፎም ትብብር መንፈግ የመንግስትን የፖለቲካ ኃይል ክምንጩ ለማድረቅ እና መንግስትን ከስልጣን ለማውረድ መድሃኒት ነው። ትብብር መንፈግ የተባለው የሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያ ማስተላለፍ የሚፈልገው መልዕክት "እኛ (We the People) ከዚህ በኋላ መንግስትን አንተባበርም!" የሚል ነው።

ትብብር መንፈግ የተባለው የሰላም ትግል ማራመጃ መሳሪያ አብይ ክፍል ሶስት ንኡሳን ክፍሎች አሉት። እነሱም፥ "(1) ማህበራዊ ትብብር መንፈጊያ ሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያዎች (Social non-cooperation Weapons)፣ (2) ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈጊያ ሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያዎች (Economic non-cooperation Weapons) እና (3) ፖለቲካዊ ትብብር መንፈጊያ ሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያዎች (Political non-cooperation Weapons)" የተባሉት ናቸው። አንድ ትክክለኛ ፕላን ያለው እና እነዚኽን መሳሪያዎች በጥንቃቄ መምረጥ እና መጠቀም የሚችል ሰላማዊ ትግል አምባገነን መንግስትን ማስወገድ ይችላል። ህዝብ ትብብር የሚነፍጉ ዘመቻ ማድረግ ከጀመረ በመንግስት የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ላይ ቀጥተኛ ጥቃት መፈጸም መጀመሩን አንባቢ ልብ ሊል ይገባል። የትብብር መንፈግን ሶስት ንኡሳን ክፍሎች ባጭር ባጭሩ እንመልከት።

ንኡስ ክፍል አንድ ማህበራዊ ትብብር መንፈግ የሚለው ነው። በህብረተሰብ ውስጥ ማንኛውም ሰው ማህበራዊ ትብብር መንፈግ ይችላል። ከአንድ ሰው ጋር የነበርህን ሰላምታ መለዋወጥ፣ አብሮ ቡና ቤት መሄድ፣ ቤተሰቡ ሲታመም መጠየቅ እና የመሳሰሉትን ማህበራዊ ግንኙነቶች ካቆምህ ለግለሰቡ እና ለቤተሰቹ ማህበራዊ ትብብር ነፈግህ ማለት ነው። በህዝብ ላይ በደል ከሚፈጽሙ አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣኖች ጋር የነበረን ማህበራዊ ግንኙነቶች ማቋረጥ ግለሰቦቹን እና ቤተሰባቸውን እጅግ ሊጎዳ ይችላል። ማህበራዊ ማግለል ከሚያካትታቸው የሰላም ትግል ማራመጃ መሳሪያዎች ውስጥ የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው፥ (ሀ) ግለሰቦችን ማግለል (Ostracism of

persons)፣ ምሳሌ፥ ለሙብቱ በሰላማዊ መንገድ የሚታገልን ሰው የሚገድሉ ፖሊሶች ወይንም ባለስልጣኖች የቤተ ክርስቲያን ወይንም የመስኪድ ግልጋሎት እንዳያገኙ (Excommunication) ማድረግ፣ ሃዘናቸው እና ሰርጋቸው ላይ አለመገኘት፣ (ለ) ለማህበራዊ ክንውኖች፣ ልማዶች እና ተቋሞች ትብብር መንፈግ ምሳሌ፥ የኢትዮጵያ የስፖርት ክለብ በሰራው ጥፋት ከአፍሪካ ክለብ ጨዋታዎች ቢታገድ፣ የተማሪዎች ትምህርት ማቆም። ይኽ የሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያ ስራ ላይ ሲውል በዘር እና በሃይማኖት ክፍፍል እንዳይበከል የሰላም ትግል ሰራዊት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። በዚህ ረገድ ስህተት ከተፈጸመ መንግስት ህዝብን ለመከፋፈል እና ትግሉን ለማዳከሚያ ፕሮፖጋንዳ ይጠቀምበታል።

ንኡስ ክፍል ሁለት ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈግ ነው። ይኽ ንኡስ ክፍል ደግሞ በሁለት ይከፈላል። የመጀመሪያው ክፍል የንግድ ግንኙነት በማቋረጥ (የንግድ እገዳ ወይንም እቀባ በማድረግ) ከፖለቲካ ባላንጣ ወይንም ከፖለቲካ ባላንጣ ተባባሪ ጋር አለመገበያየት ነው። ይኽ የሰላማዊ ትግል ማራመጃ መሳሪያ ስራ ላይ ሲውል በዘር እና በሃይማኖት ክፍፍል እንዳይበከል የሰላም ትግል ሰራዊት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማደረግ አለበት። በዚህ ረገድ ስህተት ከተፈጸመ መንግስት ህዝብን ለመከፋፈል እና ትግሉን ለማዳከሚያ ፕሮፖጋንዳ ይጠቀምበታል። ሁለተኛው ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈግ ደግሞ ስራ ማቆም (Strikes) ሲሆን 22 ያህል የሰላም ትግል መሳሪያዎች አሉት። ምሳሌ፥ የእርሻ፣ የኢንዱስትሪ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የትራንስፖርቴሽን (የባቡር፣ ያቶቢስ፣ የታክሲ፣ የአየር መንገድ፣ ወ.ዘ.ተ.)፣ የማዕድን፣ የመንግስት መስሪያ ቤት (ቢሮክራሲ)፣ ወ.ዘ.ተ. ሰራተኞች ለየብቻቸው ወይንም በህብረት የሚያደርጉት የስራ ማቆም። ይኽ ሰላማዊ ትግል ቀጣይነት ካለው መንግስትን ያደኸያል። ይኽ ከሆነ ደግሞ መንግስት ለወታደሩ፣ ለጦሩ፣ ለቢሮክራሲው፣ ለካድሬው የሚከፍለው ደሞዝ በማጣት እና እንደቀድሞው መግዛት ያቅተዋል።

ንኡስ ክፍል ሶስት ደግሞ ፖለቲካዊ ትብብር መንፈግ ነው። ይኽ ንኡስ ክፍል 38 ያህል የሰላም ትግል መሳሪያዎች አሉት። ለናሙና ያህል ጥቂት እንመልከት። (ሀ) የፖለቲካ ታማኝነትን ከመንግስት ነፍጎ ለተቃዋሚ መለገስ (Rejection of authority)፣ ምሳሌ፣ ዜጎች በየድረ ገጹ፣ በየመጽሐፉ፣ በየመጽሔቱ እና በየጋዜጣው ላይ የሚፅፉት የፖለቲካ ትችት፣ ኩነና እና የትግል ቅስቀሳ። የአገር ውስጥ የመንግስት ወታደራዊ እና ሌሎች ባለስልጣኖች እንዲሁም በውጭ የሚሰሩ ዲፕሎማቶች ስልጣናቸውን እየለቀቁ ሰላማዊ ትግሉን መቀላቀላቸው። ወ.ዘ.ተ. (ለ) ዜጎች ለመንግስት የፖለቲካ ትብብር ሲነፍጉ (Citizens' non-cooperation with government)፣ ምሳሌ፣ ዜጎች በምርጫ ወቅት ድምጻቸውን በስልጣን ላይ ለሚገኘው ፓርቲ በመንፈግ ለተቃዋሚ ፓርቲ ሲለግሱ። ዜጎች ነፃነታቸውን አውጀው በሚሊዮኖች ሆነው በአደባባይ መንግስት ከስልጣን እንዲወርድ ሲጠይቁ። ወ.ዘ.ተ. (ሐ) የመንግስት ሰራተኞች ለመንግስት የፖለቲካ ትብብር ሲነፍጉ (Government personnel's non-cooperation with government)፣ ምሳሌ፥ የአስተዳደር ስራ በተገቢ አለመስራት፣ የጸጥታ ክፍል ሙሉ ትብብር ሲነፍግ፣ ፖሊስ ፈልገህ እሥር የተባለውን ግለሰብ እያየ እንዳላየ ሲሆን፣ ፖሊስ ግደል ሲባል ከመግደል ወደ ሰማይ ሲተኩስ ወይንም እንቢ ሲል። ወ.ዘ.ተ. (መ) የአለም አቀፍ መንግስታት ለመንግስት የፖለቲካ ትብብር መንፈግ (International governmental action)፣ ምሳሌ፥ አለም አቀፍ ህብረተሰብ በስልጣን ላይ ለሚገኝ መንግስት ህጋዊ ዲፕሎማሲያዊ እውቅናን ሲያዘገይ ወይንም ሲነፍግ ወይንም ሲገፍ ወይንም ሲያቋርጥ።

ጣልቃ መግባት (intervention) የተባለው ሶስተኛው አብይ የሰላም ትግል መሳሪያ ማራመጃ ክፍል አምስት ንኡሳን ክፍሎች ያሉት ሲሆን በአምስቱ ንኡሳን ክፍሎች ውስጥ ደግሞ ድምራቸው ከ40 በላይ የሚሆኑ ሰላማዊ መታገያ መሳሪያዎች አሉ። እነዚኽ የሰላም ትግል መሳሪያዎች በግልጽ የሚታዩ ናቸው። ለባለስልጣኖችም የሚደቅኑት ፈተና ቀጥተኛ በመሆኑ ፈጥኖ መልስ የማግኘት እድላቸው ከፍተኛ ነው። ከባለስልጣኖች የሚሰነዘረው ምላሽ ወከባ እና ቅጣት ሊሆንም ይችላል። ትብብር ከመንፈግ የሰላም ትግል መሳሪያዎች ይልቅ ጣልቃ መግባት የሰላም ትግል መሳሪያዎች አምባገነኖችን ይበልጥ ሊያስቆጣ እና ፈጣን ቅጣት ሊያስከትልም እንደሚችል የሰላም ትግል መሪዎች ሊገነዘቡ ይገባል። ጥቂት ምሳሌዎች እንመልከት፥ (ሀ) ሳይኮሎጂያዊ ጣልቃ ገብነት (Psychological intervention) ምሳሌ፥ የረሃብ አድማ በማድረግ ዲፕሎማቶች የመንግስት ባለስልጣኖችን እንዲያስጨንቁ ማድረግ ወ.ዘ.ተ. (ለ) አካላዊ ጣልቃ ገብነት (Physical intervention) ምሳሌ፥ የካይሮ ሰላም ትግል ሰራዊት ጥያቄው እስኪመለስ ድረስ በነጻነት አደባባይ የድንኳኖች ከተማ መስርቶ መኖሩ (Sit-ins) ድረስ መኖር፣ (ሐ) ኢኮኖሚያዊ ጣልቃ ገብነት (Economic intervention) ምሳሌ፥ የባለስልጣኖች ገንዘብ እና ንብረት እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ፣ ወይንም አማራጭ ገበያ መጠቀም መጀመር፣ ምሳሌ በአላባማ አሜሪካ ሮሳ ፓርክስ በቀሰቀሰችው የሰላም ትግል አፍሪካዊ አሜሪካውያን በህገ መንግስት የተጻፈው የእኩልነት መብታቸው እስኪከበር ድረስ በመንግስት አውቶቢስ ከመጓዝ ፈንታ አማራጭ ትራንስፖርት በመጠቀም የከተማው መንግስት ገቢ ዝቅ እንዲል ማድረጋቸው ወ.ዘ.ተ. (መ) ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት (Political intervention) ምሳሌ፣ የመንግስት አስተዳደር በስራ እንዲወጠር እና የእለት ከእለት ስራውን መስራት እንዳይችል ማድረግ፣ የሰላዮችን ስም ይፋ ማድረግ። የሰላዮች ስም ይፋ ሲደረግ ስህተት እንዳይፈጸም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ትይዩ መንግስት (Parallel government) መመስረት እና ሌሎች የፖለቲካ ጣልቃ ገብነቶች ማድረግም ይቻላል እንደ

አስፈላጊነታቸው። በኢትዮጵያ ምርጫ ሲደረግ መንግስት ድምጽ ማጭበርበር የለመደበት በመሆኑ ከአሜሪካ እና ከምዕራብ አውሮፓ ብዙ ምርጫ ታዛቢዎች በኢትዮጵያ ምርጫ ጣልቃ እንዲገቡ ማድረግ፣ እንዲሁም የሊቢያ ህዝብ ሰላማዊ ትግል እንደጀመረ ጋዳፊ በሊቢያ ህዝብ ላይ ጦርነት ሲያውጅ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያስተላለፈው ውሳኔ አስፈላጊ የሆነ የአለም ህብረተሰብ ዲፕሎማሲያዊ እና ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ነው። ቀጥለን ለጥቂት ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ጥናታችንን እንቋጫለን።

በዚህ ጽሑፍ ሰላማዊ ትግል ብለን የምንጠራው እና የምናጠናው በስትራተጂስቱ ጋንዲ የዳበረው እና ዛሬ ደግሞ እነ ጂን ሻርፕ እና ሌሎች አያሌ የአልበርት አነስታይን የሰላም ትግል ምርምር ተቋም የፖለቲካ ሳይንስ ጠበብቶች ከፍተኛ ደረጃ ያደረሱትን በተግባር የተፈተነ ሰላማዊ ትግል ንድፈ አሳብ እና አፈጻጸም ነው።

አንዳድ ሰዎች ሰላማዊ ትግል እና ትጥቅ ትግል ተደጋጋፊ ናቸው ብለው ሲሰብኩ እንሰማለን። እውነቱ ግን ተቃራኒው ነው። እነዚህ ሁለት የትግል ስልቶች ተደጋጋፊዎች አይደሉም። ሰብዓዊ መብት የሚያከብር ሰላማዊ ትግል እና በግድያ የሚያምን ትጥቅ ትግል እንዴት ተደጋጋፊ ሊሆኑ ይችላሉ? እንዲያውም ትጥቅ ትግል ሰላማዊ ትግልን ስለሚበክል የሰላም ትግል ሰራዊት አደባባይ ሲወጣ የሰው ደም ማፍሰስ የሚያስደስታቸው ወይንም በመንግስት አረመኔ ተግባር የተበሳጩ የዋሆች ወይንም በትጥቅ ትግል እምነት የተወናበዱ በውስጡ ሰርገው በመግባት በፖሊስ ላይ ግድያ ፈጽመው ሰላማዊ ትግሉን እንዳያስመቱት ጥንቃቄ እንዲያደርግ እንመክራለን። የታጠቁት ግለሰቦች ቀደም ብለው የተዘጋጁበት ጉዳይ ስለሆነ ጥቂት ጥይቶች ተኩሰው በፖሊስ ላይ ጉዳት ካደረሱ በኋላ ሮጠው ያመልጣሉ። ፖሊስ በምላሽ የሚለቀው የጥይት እሩምታ የሚያርፈው ግን በህግ አክባሪው ሰላማዊ ሰልፈኛ ላይ ነው። ሞርሲ ከስልጣን ከወረደ በኋላ በግብጽ በተደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች ያየነው ይኸንኑ ነው። መንግስት ህግ አክብረው ሰልፍ ለሚወጡ ዜጎች ጥበቃ የማድረግ ህገ-መንግስታዊ ግዴታ አለበት።

እነዚሁ የትጥቅ ትግል አራማጆች ውስጥ አንዳንዶች በድፍረት ካለምንም ሃፍረት ሰላማዊ ትግል ብቻውን አምባገነን ገዢዎችን ከስልጣን ያወረደበት አገር የለም በማለት ይጽፋሉ። ይሰብካሉ። ሃቁ ግን ተቃራኒው ነው። የግብጹ ሙባረክ፣ ከስልጣን የተወገደው በሰላማዊ ትግል መሆኑን ከመቼው እንደረሱት የሚገርም ነው። ሲጽፉ አውቀው ረስተውት ይሆናል።

ረቀቅ ያሉት የዚሁ የትጥቅ ትግል አራማጅ ክፍል ሰዎች ደግሞ ዴሞክራሲን በመጨመር ሰላማዊ ትግል ብቻውን አምባገነን ከስልጣን አውርዶ ዴሞክራሲ ያስገኘባቸው አገሮች ስለመኖራቸው የታሪክ መረጃ ስለመኖሩ እንደሚጠራጠሩ ሲሰብኩ እንሰማለን። እውነቱ ግን ተቃራኒው ነው። ብራዚል ዴሞክራሲ አገር የሆነችው በትጥቅ ትግል ወይንም በከተማ የትጥቅ አመጽ ሳይሆን ዛሬ እነ አንድነት በኢትዮጵያ በሚያካሂዱት ሰላማዊ ትግል አይነት ነው አምባገነን አስወግዳ ወደ ዴሞክራሲ ሽግግር ያደረገችው። እርግጥ በአቅም ደረጃ የኢትዮጵያው ገና በወጣትነት እድሜው ላይ ነው። ከፍተኛ የአቅም ግንባታ ዘመቻ ይጠበቅበታል። ምስራቅ አውሮፓ አገሮችም አምባገነኖችን አስወግደው ዴሞክራሲ የሆኑት በትጥቅ ትግል አይደለም። ሰርቢያ አምባገነኑን ሞልሶቪች ከስልጣን አስወግዳ ወደ ዴሞክራሲ ሽግግር ያደረገችው በትጥቅ ትግል አይደለም። የሞሊሶቪች መንግስት በስልጣን ላይ ሳለ እና ከስልጣን ከተወገደ በኋላ በህብረት ስለሚያደርጉዋቸው እና መቼ ነፃ ምርጫ እንደሚጠሩ በሚያስማማቸው ፕሮግራም ዙሪያ አስራ ስድስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህብረት መሰረቱ። በህበረት ህገ-መንግስት የማስከበር ሰላማዊ ትግል ጀመሩ። ምርጫ ሲመጣ በህብረት ተወዳደሩ። ድምጻቸው ሲሰረቅ ደግሞ በህብረት ሆነው "የህዝባቸውን ድምጽ ያስከበረ" ሰላማዊ ትግል አደረጉ። ደምጽ ለማስከበር ያደረጉት ሰላማዊ ትግል የሞሊሶቪችን መንግስት የፖለቲካ ኃይል ምንጭ አደረቀ። የፖለቲካ ኃይሉ በግልጽ ሲደርቅ ያስተዋሉት የቀድሞ ታማኞቹ የፖሊስ እና የጦር ኃይል ሹማምንት ሳይቀሩ ከዱት። ሞሊሶቪች ሽንፈቱን ከመቀበል የተሻለ አማራጭ እንደሌለው አምኖ ሽንፈቱን በሰላም እንዲቀበል አደረጉ። ከዚያ ከምርጫው በፊት በተስማሙት መሰረት ሰርቢያን ለሶስት ወይንም ለአራት አመቶች ያህል ጊዜ በህብረት ከገዙ በኋላ በሰርቢያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃ ምርጫ ጠርተው 16ቱ ፓርቲዎች ተፎካከሩ። አብዛኛውን የህዝብ ድምጽ ያገኘው ፓርቲ ገዢ ፓርቲ ሲሆን የቀሩት ተቃዋሚ ፓርቲ በመሆን የፓርላማ ትግል ጀመሩ። የሰርቢያ ዴሞክራሲ አራማጅ ፖለቲከኞች ይኸን ሁሉ ሰላማዊ ትግል ሲያደርጉ አንድም ቀን ስለትጥቅ ትግል ተወያይተውም አያውቁም። እርግጥ የሰርቢያ ተቃዋሚዎች FM ሬዲዮ ነበራቸው። ስለዚህ ሰላማዊ ትግል በፍጹም ከማንኛውም አይነት ትጥቅ ትግል ወይንም የከተማ የትጥቅ አመጽ እርዳታ እና ትብብር እንደማይሻ ከወዲሁ በማክበር እናስታውቃለን። ሰላማዊ ትግላችን በጠብ መንጃ፣ በቦንብ፣ በታንክ፣ በመድፍ እና በመሳሰሉት የግድያ መሳሪያዎች እንዲበከልብን አንፈልግም። ይኸን ልዩነት አንባቢ ሊገነዘብ ይገባል።

በመጨረሻ አንድ መንግስት ካለ ህዝብ ታዛዥነት (Obedience)፣ ትብብር (Cooperation) እና አሜን ብሎ መገዛት/መገበር (Submission) በስልጣን ሊቆይ እንደማይችል የዝንጀሮዎች ጌታ ማስረጃ መሆኑን ለአንባቢ በማስታወስ የዛሬውን ጥናታችን እንደመድማለን።